በጉምሩክ ኮሚሽን
የአዲስ አበባ ቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት
CUSTOMS COMMISSION
ADDIS ABABA KALITI CUSTOMS BRANCH OFFICE

ቁጥር: ስ/አ/ጽ/ቤት/46/2011
ቀን: 27/03/2011

- ለ: ህግ ህግ ተገዥነት ም/ስራ አስኪያጅ
- ለ: ህግ ማስከበር የስራ ሂደት
- ለ: ቱሉ ዲምቱ ጉምሩክ መቆጣጠሪያ ጣቢያ
- ለ: አቃቂ ቃሊቲ ጉምሩክ መቆጣጠሪያ ጣቢያ

- ከ: ስራ አስኪያጅ ጽ/ቤት (አለማየሁ አንቲቾ)

አዲስ አበባ ቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት

ጉዳዩ:- **በኦሮሚያ፣ በሶማሌ እና በአፋር ክልሎች ያለውጭ ምንዛሬ ፈቃድ ከቀረጥ ነፃ እንዲገቡ የተፈቀደበት መመሪያ በሥራ ላይ መዋሉ እንዲቆም የተወሰነውን ይመለከታል፣**

ከጉምሩክ ኮሚሽን ኮሚሽነር በቁጥር 4.0/143/11 በህዳር 24 ቀን 2011 ዓ.ም ለቅርንጫፍ ጽ/ቤታችን በተጻፈ ደብዳቤ መሠረት በኦሮሚያ፣ በሶማሌ እና በአፋር ክልሎች በሚገኙ አንድ አንድ የጠረፍ ወረዳዎች ነዋሪ ለሆነው ህብረተሰብ እንዲውሉ ከውጭ የሚቀርቡ መሠረታዊ የምግብ አቅርቦቶችና የባህል አልባሳት ያለውጭ ምንዛሬ ፈቃድ ከቀረጥ ነፃ እንዲገቡ የተፈቀደበት መመሪያ በሥራ ላይ መዋሉ እንዲቆም የተገለፀልን ስለሆነ፣ በውሳኔው መሠረት እንዲፈጸም አሳውቃለሁ። ለግንዛቤ ይረዳችሁ ዘንድ 4 ገጽ አባሪ ተያይዟል።

ከሠላምታ ጋር

ግልባጭ፣

- ለንግድ ዕቃዎች ኦፕሬሽን ም/ስራ አስኪያጅ
- ለአምራች ውጪና ገቢ ዕቃዎች ም/ስራ አስኪያጅ

አዲስ አበባ ቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ፅ/ቤት

ስልክ
0118964720

- የተገልጋዮች ድጋፍና አጠቃላይ ቅሬታ ማስተናገጃ የስራ ክፍል ምላሽ የማይሰጡ ወኪሎችን የዕቃ አወጣጥ ዩኒቶች ሲያሳውቁ እርምጃ ከመውሰድ አንፃርና መመሪያውን ተግባራዊ ከማድረግ ክፍተት ያለባቸው መሆኑ፣
- የተቋሙ 8:00 የስራ ሰዓት ስራ ላይ እየዋለ አለመሆኑ(ማሳያ በውስጥ ማስታወሻ የተከማቹ ሰነዶች ከነ ምክንያታቸው ተገልጾ እንዲላክልን መስከረም 29/2011 ተጠይቆ እስከ 03/02/2011 ዓ.ም በ4 ቀን ተግማሽ በሰባቱ ክሊራንስ ዩኒቶች 803 ሰነድ የተበተነ መሆኑ)፣
- የተቋሙ ህጋዊ መመሪያዎች እና የአሰራር ስርዓት እየተከበረ አለመሆኑ(ማሳያ መመሪያ ቁጥር 64/03፣የአደራ የውጪ ፍተሻ ላይ መመሪያ ቁጥር 119/2008 ተግባራዊ እየተደረገ አለመሆኑ)፣
- ከተጓደኛ መ/ቤት ጋር ተያይዞ መረጃ መቅረብ እየለበት በወቅቱ ባለመቅረቡ ለምሳሌ፡- የቡና ውጤት ማሰወቂያ ሰርተፊኬት ኦርጅናሉን አሰይተው ኮፒ እነመጣለን በማለት ሳያመጡ በመቅረታቸው ሰነድ ሳይበተን እንዲከማች ማድረግ፣
- በተቀያሪ ኬሻ በገኘው ትዕዛዝ ተጠይቆ የተቀየረው ኬሻ ስለመመለሱ ማረጋገጫ ባለመቅረቡ ሰነድ ሳይበተን የሚቆይ መሆኑ፣
- Registered but not assessed፣ assessed ሆነው ተቀባይነት ያላገኙ እና ተቀባይነት አግኝተው T1 ያልተዘገጀለቸው(ከሀገር ስለመውጣታቸው) ማስረጃ ያልቀረበላቸው የቆዩ ሰነዶች መኖረቸው፣
- ተቋሙ አምኖበት የዘጋጀውን የዜጎች ቻርተር በየደረጀው ያለ አመራርም ሆነ ፈፃሚ እርምጃ እየተወሰደ ባለመሆኑ ተግባራዊ እያደረገው አለመሆኑ፣
- በተለያዩ ምክንያቶች በቅሬታ ላይ ያሉ ሰነዶች ለረዥም ዓመት ውሳኔ እየተሰጠ ባለመሆኑ ሰነድ ተከማችቶ የሚቆይ መሆኑ፣
- ከአዲሱ ሲስተም ጋር ተያይዞ በከፊል የሚለቀቁ ሰነዶች በጊዜያዊ ዕቃ ማከማቻ መጋዘን ቡድን በኩል ዕቃዎቹ ተጠቃለው በሚገቡበት ወቅት የመጨረሻውን የማመጣጠን ስራ በሲስተም ላይ ባለመሰራቱ ወይም ትኬት ባለመዘጋጀቱ ሰነድ ለመበተን አለመቻሉና ሰነዱ ቢበተን በሲስተም ላይ ፓርሻል ሆኖ ስለሚያሳይ ይህም ለሰነዶች መከማቸት ዋነኛ ምክንያት እየሆነ ያለበት ሁኔታ መኖሩ፣
- በመመሪያ ቁጥር 118/08 አንቀጽ 18 መሰረት ሰነድ ከተበተነ በኋላ ሰነድ እንዲታረም ተፈቅዶ እያለ አዲሱ ሲስተም ሰነድ ከተበተነ በኋላ ሲስተሙ አለመፍቀዱ እየታወቀ በተቃራኒው ደግሞ ቀረጥና ታክስ የተከፈለበትና ዕቃው መልቀቂያ ከተሰጠው በኋላ

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ በገቢዎች ሚኒስቴር
የጉምሩክ ኮሚሽን

Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Revenues
Customs Commission

ቀን 24 ህዳር 2011
Date
ቁጥር 21-0/148/11
Ref. No.

ለየጉምሩክ ሥነ-ሥርዓት ለሚፈፀምባቸው ቅ/ጽ/ቤቶች በሙሉ

<u>በያሉበት፣</u>

ጉዳዩ፡- <u>በኦሮሚያ፣ በሶማሌና በአፋር ክልሎች በሚገኙ አንድ አንድ የጠረፍ ወረዳዎች ነዋሪ ለሆነው ህብረተሰብ እንዲውሉ ከውጭ የሚቀርቡ መሠረታዊ የምግብ አቅርቦቶችና የባህል አልባሳት ያለውጭ ምንዛሪ ፈቃድ ከቀረጥ ነፃ እንዲገቡ የተፈቀደበት መመሪያ በሥራ ላይ መዋሉ እንዲቆም መወሰኑን ስለማሳወቅ፣</u>

በጠረፍ አካባቢዎች የመሠረተ ልማት ውስንነት የሚፈጥረውን የምግብ ሸቀጦችና የባህል አልባሳት አቅርቦት እጥረት ችግር ለማቃለልና በእነዚህ አካባቢዎች ነዋሪ የሆነው ህበረተሰብ እነዚህን መሠረታዊ አቅርቦቶች በአነስተኛ ዋጋ ሸምቶ እንዲጠቀም ለማስቻል፣ የህገ-ወጥ ንግድ ተፅዕኖን ለማስወገድ በማሰብ በአገራችን በአንድ አንድ የጠረፍ አካባቢዎች ለሚኖሩ ዜጐች የሚያገለግሉ መሠረታዊ የምግብ አቅርቦቶችና የባህል አልባሳት ያለውጭ ምንዛሪ ፈቃድ (በፍራንኮ ቫሉታ) ከቀረጥና ታክስ ነፃ ከውጭ እንዲገቡ የሚፈቅድ መመሪያ የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ህዳር 1 ቀን 2007 ዓ.ም. እንዲሁም ይህንኑ መመሪያ የሚያሻሽሉ መመሪያዎች ግንቦት 01 ቀን 2007 ዓ.ም. እና መስከረም 15 ቀን 2009 ዓ.ም. ማስተላለፉን በመግለፅ እና መመሪያው የታሰበለትን ዓላማ በማሳካት ህብረተሰቡን ተጠቃሚ ከማድረግ ይልቅ ህገ-ወጥ ንግድን በማስፋፋት በአገር ውስጥ የንግድ ውድድር ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ እያሳደረና ለውጭ ምንዛሪ ጥቁር ገበያ መስፋፋት ምክንያት መሆኑን በመግለፅ በመመሪያው የተፈቀደውን የቀረጥና ታክስ ልዩ መብት ማንሳት ተገቢ መሆኑን እና እንዲሁም ይህ መመሪያ ከተላለፈበት ቀን በፊት ወደ አገር ውስጥ ለመግባት በመንገድ ላይ ያሉ የምግብ ሸቀጦችና የባህል አልባሳትን ሳይጨምር ከህዳር 19 ቀን 2011 ዓ.ም ጀምሮ በኦሮሚያ፣ በሶማሌና በአፋር ክልሎች ለሚገኙ የተወሰኑ የጠረፍ ወረዳዎች ነዋሪ ለሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች ፍጆታ እንዲውሉ ከውጭ የሚቀርቡ መሠረታዊ የምግብ ሸቀጦችና የባህል አልባሳት ያለውጭ ምንዛሪ ፈቃድ ከቀረጥና ታክስ ነፃ እንዲገቡ የተፈቀደበትን መመሪያ ቁጥር 40/2007 (ከነማሻሻያዎቹ) በሥራ ላይ መዋሉ እንዲቋረጥ የተወሰነ ስለመሆኑ የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር በቁጥር 7/ኢ/1/2/286 በቀን 19/03/2011 ዓ.ም. በተፃፈ ደብዳቤ አሳውቆናል።

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር
The Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of Finance and Economic Cooperation

ቁጥር
Ref No. 7/ፚ/1/2/286
ቀን
Date 19/3/2011

ለገቢዎች ሚኒስቴር
<u>አዲስ አበባ</u>

በጉዳዩ:- በኦሮሚያ፣ በሶማሌና በአፋር ክልሎች በሚገኙ አንድ አንድ የጠረፍ ወረዳዎች ነዋሪ ለሆነው ህብረተሰብ እንዲውል ከውጭ የሚቀርቡ መሠረታዊ የምግብ አቅርቦቶችና የባህል አልባሳት ያለውጭ ምንዛሪ ፈቃድ ከቀረጥ ነፃ እንዲገቡ የተፈቀደበት መመሪያ <u>በሥራ ላይ መዋሉ እንዲቆም መወሰኑን ስለማሳወቅ፣</u>

በጠረፍ አካባቢዎች የመሰረተ ልማት ውስንነት የሚፈጥረውን የምግብ ሸቀጦችና የባህል አልባሳት አቅርቦት እጥረት ችግር ለማቃለልና በእነዚህ አካባቢዎች ነዋሪ የሆነው ህብረተሰብ እነዚህን መሰረታዊ አቅርቦቶች በአነስተኛ ዋጋ ሸምቶ እንዲጠቀም ለማስቻል፣ በሕገ-ወጥ መንገድ ወደአገር ውስጥ በሚገቡ ደረጃቻቸውን ባልጠበቁ የምግብ ምርቶች ምክንያት በህብረተሰቡ ላይ የሚደርሰውን የጤና ችግር ለመከላከል እና በጠረፍ አካባቢ ያለውን የሕገ-ወጥ ንግድ ተፅህኖን ለማስወገድ በማሰብ በአገራችን በአንድ አንድ የጠረፍ አካባቢዎች ለሚኖሩ ዜጎች የሚያገለግሉ መሠረታዊ የምግብ አቅርቦቶችና የባህል አልባሳት ያለውጭ ምንዛሪ ፈቃድ (በፍራንኮ ቫሉታ) ከቀረጥና ታክስ ነፃ ከውጭ እንዲገቡ የሚፈቅድ መመሪያ መ/ቤታችን ህዳር 1 ቀን 2007 ዓ.ም እንዲሁም ይህንኑ መመሪያ የሚያሻሽሉ መመሪያዎች ግንቦት 1 ቀን 2007 ዓ.ም እና መስከረም 15 ቀን 2009 ዓ.ም ማስተላለፉ ይታወቃል::

መመሪያው የታሰበበትን ዓላማ እያሳካ መሆኑን ለማረጋገጥ ከኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን እና ከንግድ ሚኒስቴር የተውጣጣ የጥናት ቡድን ተቋቁሞ ቡድኑ የፈቃዱ ተጠቃሚ በሆኑ ክልሎች በሚገኙ የጠረፍ ወረዳዎች ነዋሪ ከሆነው ህብረተሰብ፣ ከአቅራቢዎችና ከቸርቻሪ ነጋዴዎች ጋር ውይይት በማድረግ እንዲሁም ከኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ቅ/ጽ/ቤቶች፣ ከየክልሉ የንግድ ቢሮዎች፣ ከንግድ ሚኒስቴርና ከኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን መረጃዎችን በመሰብሰብ የመመሪያውን አፈፃፀም መገምገም የሚያስችል ጥናት አካሄዷል:: በተደረገው ጥናት መንግሥት ህብረተሰቡን ተጠቃሚ ለማድረግ ሲባል ከቀረጥና ታክስ ሊሰበስብ ይችል የነበረውን ከፍተኛ ገቢ ሳይሰበስብ ቢቀርም ህብረተሰቡ በአቅርቦትና በዋጋ ረገድ በአግባቡ ተጠቃሚ አለመሆኑን፣ ስርዓቱ እንደተጠበቀው የኮንትሮባንድ ንግድን ከመከላከል ይልቅ ለሕገ -ወጥ ንግድ አመቺ ሁኔታን በመፍጠር ፍትሐዊ ያልሆነ የገበያ ውድድር እንዲኖር በማድረግ በአገር ውስጥ አምራቾች ላይ ከፍተኛ ጉዳት ማስከተሉን፣ ለውጭ ምንዛሪ የጥቁር ገበያ መስፋፋት ምክንያት በመሆን በሕጋዊ የውጭ ምንዛሪ አቅርቦት ላይ አሉታዊ ውጤት እያስከተለ መሆኑን፣ የመመሪያው አፈፃፀም፣ ክትትልና ቁጥጥር በተጠበቀው ደረጃ አለመሆኑን፣ ከፍትሐዊ ተጠቃሚነት አኳያ መመሪያውን የጠረፍ አካባቢዎች ባሉባቸው ክልሎች ሁሉ ተፈፃሚ ማድረግ ተገቢ ቢሆንም ይህንን ማድረግ በአገሪቱ የንግድ ሥርዓት ላይ ከፍተኛ ችግር የሚያስከትል መሆኑን እንዲሁም በመመሪያው የተዘረጋው ሥርዓት በጎረቤት

Ethiopian Customs Commission
Record & Documentation

Letter/Hb/TA

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር
The Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of Finance and Economic Cooperation

ቁጥር Ref.No 1/ከ1/12/286
ቀን Date 19/3/2011

አገሮች መካከል በሚደረግ ስምምነት መሠረት ተግባራዊ የሚደረገውን የድንበር ንግድ አሠራርን የማይተካ መሆኑን ማረጋገጥ ተችሏል።

በፍራንኮ ቫሉታ ቀረጥና ታክስ ነፃ መመሪያ ቁጥር 40/2007 አንቀጽ 8 የተፈቀደው የቀረጥና ታክስ ልዩ መብት ለሕዝብ የተፈለገውን ጥቅም የማያስገኝ መሆኑ ሲረጋገጥ መብቱ በማናቸውም ጊዜ ሊቋረጥ እንደሚችል ተደንግጓል። በተደረገው ጥናት መመሪያው የታሰበለትን ዓላማ በማሳካት ህብረተሰቡን ተጠቃሚ ከማድረግ ይልቅ ሕገ-ወጥ ንግድን በማስፋፋት በአገር ውስጥ የንግድ ውድድር ላይ አሉታዊ ተጽህኖ እያሳደረና ለውጭ ምንዛሪ ጥቁር ገበያ መስፋፋት ምክንያት መሆኑን ማረጋገጥ የተቻለ በመሆኑ በመመሪያው የተፈቀደውን የቀረጥና ታክስ ልዩ መብት ማንሳት ተገቢ መሆኑ ታምኖበታል።

ስለዚህ ይህ መመሪያ ከተላለፈበት ቀን በፊት ወደ አገር ውስጥ ለመግባት በመንገድ ላይ ያሉ የምግብ ሸቀጦችና የባህል አልባሳትን ሳይጨምር ከህዳር 19 ቀን 2011 ዓ.ም ጀምሮ በኦሮሚያ፣ በሶማሌና በአፋር ክልሎች ለሚገኙ የተወሰኑ የጠረፍ ወረዳዎች ነዋሪ ለሆኑ የህብረተሰብ ክፍሎች ፍጆታ እንዲውሉ ከውጭ የሚቀርቡ መሠረታዊ የምግብ ሸቀጦችና የባህል አልባሳት ያለውጭ ምንዛሪ ፈቃድ ከቀረጥና ታክስ ነፃ እንዲገቡ የተፈቀደበት መመሪያ ቁጥር 40/2007 (ከነማሻሻዎቹ) በሥራ ላይ መዋሉ እንዲቋረጥ የተወሰነ መሆኑን አስታውቃለሁ።

ከሠላምታ ጋር

አህመድ ሺዴ
ሚኒስትር

ግልባጭ፣

ለጉምሩክ ኮሚሽን
ለንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር
አዲስ አበባ

ስልክ Tel 251-11-155 24 00 / 22 66 36
ፖ.ሣ.ቁ P.O.Box 1905/1037
ፋክስ Fax 251-11-155 01 18 / 55 14 85
251-11-155 33 03 / 22 33 20
251-11-155 31 14
አዲስ አበባ ኢትዮጵያ Addis Ababa Ethiopia

በዚሁ መሠረት መመሪያው ከተላለፈበት ከህዳር 19 ቀን 2011 ዓ.ም ጀምሮ ውሳኔው ተፈፃሚ እንዲሆን አሳስባለሁ፡፡

ከሠላምታ ጋር

በሌ ቃበታ ሁሩሳ
ጉምሩክ ኮሚሽን ኮሚሽነር

ግልባጭ፡-

- ለገቢዎች ሚኒስቴር
- ለገንዘብና ሚኒስቴር
- ለኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ንግድ ቢሮ
- ለአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ንግድ ቢሮ
- ለሱማሌ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ንግድ ቢሮ

  በያሉበት፣
- ለጉምሩክ ኦፕሬሽን ዘርፍ
- ለጉምሩክ ህግ ተገዥነት ዘርፍ

  ጉምሩክ ኮሚሽን፣